# ጉባዔ-ሁለት

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

# SERMON-2

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

# ከጉባዔ-አንድ ለማስታወስ

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።




# አሮጌውን በር እናድስ!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## የትምህርቱ ዓላማ፤

፩ኛ-እግዚአብሔርን ማወቅ በራሱ ሕይወት ስለሆነ ለአምልኮ እንዲያግዘን፤

፪ኛ-የወልደ እግዚአብሔርን አምላክነቱን አዳኝነቱን ሰፋ አድርጎ ለማየት፤እና

፫ኛ-የቤተክርስቲያናችንን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራዕይ ለመደገፍ፡፡



## የትምህርቱ ዓላማዎች.....በሌላ አገላለጽ

† የትምህርቱ ዓላማዎች (በዋናነት)

- የቀደመውን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሃሳብ መለስ ብሎ በማየት፤ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፥ ሴይጣን ዉሸተኛ ለማለት፥
- መዳናችንን በማስረገጥ ፣ የድነትን ጽንሰ ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስረዳት፤ ከተለመደዉ ዓይነትም ወጣ ብሎ የነገረ-ድነት ማጣቀሻ ጽሑፍ ለሚማርም ፥ ለሚያስተምርም ለማቅረብ፥
- ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በቃል ስለምንሰጠው ምስክርነት ግንዛቤያችንን ለማስፋት ፥ እና
- ከዘፍጥረት 1-3 ያሉትን ዋና ሃሳቦች አጉልቶ በማሳየት ፤ የዘፍጥረት መጀመሪያው አምላክ ፤ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስም ሁሉ አምላክ እንደሆነ በመግለፅ ላይ አነጣጥሯል።



† የትምህርቱ ዓላማዎች (ከግንዛቤ በማስገባት)፡

- ቀደም የተረዳነዉን እዉነት ለማጠናከር፥ የረሳነዉን ለማስታወስ፥ የተሳሳትነዉን ለማረም፥ ያላወቅነዉንም ለማሳወቅ ነው፤ ስለዚህ ሁላችንም ተማሪዎች ነን!
- ተናጋሪዉንና አነጋገሩን ሳይሆን የሚነገረዉን እዉነት ልክ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ በመመዘን ከተቻለ ሁሉንም ፥ ካልሆነ ከፊሉን መቀበል ብልህነት ሲሆን፥ ሁሉንም አለመቀበል ደግሞ የራስ መብት ነዉ።



† ትምህርቱ የቤተክርስቲያኗን መሰረታዊ አስተምሮ ፍሬም የጠበቀ ቢሆንም፤ ከሁሉ በመሻል ለማስተማር ሳይሆን፤ በመዘጋጀትም ይሁን በማቅረብ ለመማር የሚሰጥ በመሆኑ፤

✓ ይህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ትምህርቱን የማረም መብት አላት።

✓ መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ የቃላት ግድፈቶችን በማረም ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ማስገንዘቢያ

† አሮጌውን ቅጥራችን እናድስ ስንል፡-

- ✓እግዚአብሔር በዔድን ገነት የተናገረው ሁሉ እዉነት ነዉ፤ መነሻችንም ፥ መድረሻችንም እርሱ ነዉ። እያልን ነው።

- ✓አንድም ፤ የዘፍጥረቱ እግዚአብሔር የተቀረዉ መጽሓፍ ቅዱስ ሁሉ አምላክ ነው። ከዘመን በኋላም በልጁ በኩል የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። እያልን ነው።



እግዚአብሔር አብርሃምን አምላክ ይሆነዉ ዘንድ መረጠዉ..

እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።

[ዘፍ12$^{1-3}$]



እግዚአብሔር አምላክ ሊሆነዉ ከነአንን ተስፋ ሰጠዉ፤...

ወደ ሜዳም አወጣውና፡- ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው። አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው።

[ዘፍ15$^{5-7}$]



እግዚአብሔር ግዝረትን እንደ ቃል-ኪዳን ሰጠዉ፡...

ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። እጅግም አበዛሃለሁ፥ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣሉ። ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፥ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ። በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር፥ የከነዓን ምድር ሁሉ፥ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ። እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ፥ አንተ ከአንተም በኋላ ዘርህ በትውልዳቸው። በእኔና በአንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። የቍልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።

[ዘፍ17$^{7-12}$]

## እግዚአብሔር በገባዉ ቃል መሰረት እስራኤልን ከግብፅ ነጻ አወጣ…

እግዚአብሔርም አለ፡-

በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ፥ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈስሰው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ አሞራውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ስፍራ አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ፡፡[ዘጸ3^7-8]



## እግዚአብሔር ስለ ቃል-ኪዳኑ ብቻ ርስቱን አወረሳቸዉ።…

አምላክህም እግዚአብሔር እንደሚበላ እሳት ሆኖ በፊትህ እንዲያልፍ ዛሬ እወቅ እርሱ ያጠፋቸዋል፥ በፊትህም ያዋርዳቸዋል እግዚአብሔርም እንደ ነገረህ አንተ ታሳድዳቸዋለህ፥ ፈጥነህም ታጠፋቸዋለህ። አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ ካወጣቸው በኋላ። ስለ ጽድቄ እወርሳት ዘንድ ወደዚች ምድር እግዚአብሔር አገባኝ ስትል በልብህ አትናገር እነዚህን አሕዛብ ስለ ኃጢአታቸው እግዚአብሔር ከፊትህ ያወጣቸዋል። ምድራቸውን ትወርሳት ዘንድ የምትገባው ስለ ጽድቅህና ስለ ልብህ ቅንነት አይደለም ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ከፊትህ በሚያጠፋቸው በእነዚያ አሕዛብ ኃጢአት ምክንያትና ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማለላቸውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው። እንግዲህ አንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነህና አምላክህ እግዚአብሔር ይህችን መልካም ምድር ርስት አድርጎ የሰጠህ ስለ ጽድቅህ እንዳይደለ እወቅ።

[ዘዳ9^3-6]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## ነገስታት ይንገስልን የሚል ትዉልድ ይመጣ ዘንድ አለና፤ የንጉስን ሥራዓት ሰራላቸዉ…

አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ ምድር በገባህ፥ በወረስሃትም ጊዜ፥ በተቀመጥህባትም ጊዜ። በዙሪያዬ እንዳሉት አሕዛብ ሁሉ በላዬ ንጉሥ አነግሣለሁ ስትል፥ አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሣለህ ከወንድሞችህ መካከል የሆነውን በአንተ ላይ ንጉሥ ታነግሣለህ ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም። ነገር ግን ለእርሱ ፈረሶችን አያበዛም እግዚአብሔር፡- በዚያ መንገድ ደግማችሁ አትመለሱም ብሎአችኋልና ፈረሶችን ለማብዛት ሕዝቡን ወደ ግብፅ አይመልስም። ልቡም እንዳይስት ሚስቶችን ለእርሱ አያበዛም ወርቅና ብርም ለእርሱ አጅግ አያበዛም።

[ዘዳ17^14-17]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## እግዚአብሔር ሳዖልን፥ ዳዊትን አነገሰላቸዉ።…

- ለ300 ዓመታት በመሳፍንት ከመራቸዉ በኋላ፤ እንደ አህዛብ ንጉስን ያነግስላቸዉ ዘንድ ሳሙኤልን ጠየቁት፤
- እግዚአብሔርም ሳዖልን አነገሰላቸዉ።
- ሳዖል በፊቱ ፍጹም አልሆነምና እንደ ልቤ ያለዉን ዳዊትን አነገሰላቸዉ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## እግዚአብሔር ሳዖልን፥ ዳዊትን አነገሰላቸዉ።...

- ከዳዊት በኋላ ልጁን ሰሎሞንን ደግሞ አነገሰላቸዉ።
- ሰሎሞን ግን ሙሴ ያዘዘዉን ሦስቱንም የእስራኤል ነገስታት መንፈሳዊ ሥራዓቶች አፈረሰ፤
  1. ፈረሶችን አበዛ፥
  2. የአህዛብ ሴቶችን አገባ (700 ሚስቶችና፥300 ዕቁባቶችን)፥ለጣዖትም ሰገደ፥
  3. ወርቅና ብርም እጅግ አከማቸ።
- እግዚአብሔር መንግስቱን ለሁለት ቀደደዉ፤ ስለ ዳዊት ሲል ግን በልጁ በሮባም ዘመን አደረገዉ።

[1ነገ 11 1-13]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## በበረሃ እንዳመነዘሩበት አሁን ደግሞ በሁለት ዕጥፍ በቅድስናዉ ለይ አመጹበት፥ ሥራዉንና ኃይሉን ካዱ።

ሕዝቡም ሙሴ ከተራራው ሳይወርድ እንደ ዘገየ ባዩ ጊዜ፥ ወደ አሮን ተሰብስበው። ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሰው ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና ተነሥተህ በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን አሉት። አሮንም። በሚስቶቻችሁ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ በጆሮቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት። ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው እርሱም፦ እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው

[ዘጸ32 1-4]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## የሰሜኑ እስራኤል በቤቴልና በዳን ሁለት የጥጃ ምስል አቆመ

ኢዮርብዓምም በልቡ። አሁን መንግሥቱ ወደ ዳዊት ቤት ይመለሳል። ይህ ሕዝብ በእግዚአብሔር ቤት መሥዋዕትን ያቀርብ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ቢወጣ፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ወደ ጌታቸው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም ይመለሳል፥ እኔንም ይገድሉኛል አለ። ንጉሡም ተማከረ፥ ሁለትም የወርቅ ጥጆች አድርጎ። እስራኤል ሆይ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል ከግብጽ ምድር ያወጡህን አማልክቶችህን እይ አላቸው። አንዱን በቤቴል፥ ሁለተኛውንም በዳን አኖረ። ለአንዱ ጥጃ ይሰግድ ዘንድ ሕዝቡ እስከ ዳን ድረስ ይሄድ ነበርና ይህ ኃጢአት ሆነ።

[1ነገ12 26-30]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

## የአሮን ጥጃ በቁጥር ሁለት ሆኖ መጣ፤

ኃጢአቱ የእግዚአብሔርን ሥም መጥራታቸዉ ሳይሆን፤ ቀልጦ ለተሰራ ጥጃ የእግዚአብሔርን ሥም ሰጥተዉ መስገዳቸዉ ነዉ!!!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

የኢዮርባዓም ኃጢአት በዓልን ወደ ማምለክም ተሸጋገረ!

ኤልያስም ወደ ሕዝቡ ሁሉ ቀርቦ።
እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ
ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ
ቢሆን እርሱን ተከተሉ በኣል ግን
አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ።
[1ነገ18[21]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

የአሮን ጥጃ በቁጥር ሁለት ሆኖ መጣ፤
አሁን ደግሞ የበዓልን አምልኮ
ጨመረ።

እስራኤል ለጥጃ የእግዚአብሔርን
ሥም ሰጥተዉ መስገዳቸዉ ፤ ወደ
አህዛቡ ጣኦት አምልኮ ተሸጋገረ!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ነብየ እግዚአብሔር ኤልያስ ግን
የሰሜን እስራኤል ነብይ ቢሆንም
ወደቀደመዉ ተስፋ ሕዝቡን
በመመለስ እንደ እስራኤል ልጆች
ቁጥር 12 ድንጋይ በመዉሰድ ፈርሶ
የነበረውንም የእግዚአብሔርን
መሠዊያ አበጀ። [1ነገ18[30-31]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

አሮጌዉን በር እናድስ ስንልም ልክ
የእስራኤል ተስፋ እግዚአብሔር
ለአብርሃም፥ለይስሃቅም፥ለያዕቆብም
እንዳለዉ እንጂ፤ አሮን
እንዳስተማራቸዉ፥ኢዮርብዓምም
እንዳበዛዉ ጥጃዎች፥አካብም
እንደጨመረዉ የበዓል አምልኮ ሳይሆን
ለሙሴ እንደተናገረዉ ያለ ምስል
የሚመለከዉ ነዉ እያልን ነዉ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

አሮጌዉን በር እናድስ ስንል እግዚአብሔር ለሰዉ ልጅ በዔድን ገነት የተናገረዉ ሁሉ እዉነት ነዉ እያልን ነዉ።



በዚሁም መንፈስ በእግዚአብሔር ልጅ የተመሰረተችዉ ቤተክርስቲያን አንድ ብቻ ናት!! የእግዚአብሔር እዉነተኛ አገልጋይ የሆነ ሁሉ ልክ ኤልያስ 12ቱን ድንጋዮች ባነሳዉና ፈርሶ የነበረዉን የእግዚአብሔር መሰዉያ በሰራዉ ምሳሌ የቀደመዉን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አንድነት መንፈስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ማቀጣጠል ይገባዋል እያልን ነዉ።